# የተጠራቀመ የህመምና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ (ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-ESST)

## በስራ ላይ የሚውለው ጥር (Jan.) 1 ቀን 2024

### ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ምን ማለት ነው?

ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ (ESST) ማለት የሚኖሶታ አሰሪዎች ለሰራተኞቻቸው መስጠት ያለባቸው፣ ደሞዝ የሚከፈልበት የስራ ፈቃድ ማለት ሲሆን ይህ ፈቃድ ሰራተኛው እርሱ ሲታመም ወይም የቤተሰቡ አባላት ሲታመሙ ለማስታመም ወይም እርሱ ወይም የቤተሰቡ አባል በላያቸው ላይ አንድ ዓይነት የቤተዘመድ ዓመጽ (domestic abuse) ወይም በግዴታ የሚደርግ ወሲባዊ ዓመጽ/ጥቃት (sexual assault) ወይም በሚደረግ ተደጋጋሚ የመከታተል ጥቃት (stalking) ሲያጋጥም እርዳታ ለመጠየቅና ለማግኘት ግዜ ሲያስፈልግ የሚወሰድ የስራ ፈቃድ ነው።

ይህ ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) የሚከፈለው ልክ ሌላው ስራ በሰዓት እየታሰበ እንደሚከፈለው ሁሉ ይህም በሰዓት እየታሰበ የሚከፈል ነው።

### የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ፈቃድ ለማግኘት ብቁ የሚሆነው ማነው?

አንድ ሰራተኛ ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ለማግኘት ብቁ የሚሆነው፤

- በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ 80 ሰዓታት በሚኖሶታ ለሚኖር ቀጣሪ የሰራ ሲሆንና
- ለግሉ የሚሰራ ነጻ ባለኮንትራት ካልሆነ

ለዚህ ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ግዜያዊና የከፊል ግዜ ሰራተኞችም (part-time employees) ብቁዎች ናቸው።

### የበቀል እርምጃ መውሰድ ከህግ ውጪ ነው።

አንድ ሰራተኛው በኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ህግ መሰረት ያለውን ህጋዊ መብት ተጠቅሞ ፈቃድ ቢወስድ፤ አሰሪው በሰራተኛው ላይ የቂም በቀል እርምጃ ወይም ማንኛውንም ዓይነት አሉታዊ እርምጃ መውሰድ በህግ የተከለከለ ነው።

### እንዴት ነው የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) የፈቃድ ግዜ ማጠራቀምና መውሰድ የሚቻለው?

- ሰራተኞች፤ ለየሰሩባቸው 30 ሰዓታት እየተከፈሉ ቢያንስ የአንድ ሰዓት የስራ (የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ፈቃድ ያገኛሉ። ይህም የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ህግ እስከፈቀደው ድረስ አስቀድመው አሰሪዎች ካልጨመሩበት በስተቀር ማለት ነው።
- ኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) የፈቃድ ግዜ ሰራተኞች ስራ ከጀመሩበት ቀን አንስቶ መጠራቀም ይጀምራል፤ ሰራተኞችም ፈቃዱ እየተጠራቀመላቸው ሲሄድ ባፈለጉበት ግዜ ሊጠቀሙበት ይፈቀድላቸዋል።
- አሰሪዎች በየዓመቱ እያንዳንዱ ሰራተኛ ቢያንስ 48 ሰዓታት የእረፍት ግዜ (የህመመና የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ) እንዲያጠራቅም ይፈቅዳሉ። ሰራተኛው በዓመቱ ውስጥ ካጠራቀመው የእረፍት ግዜ፤ ሳይጠቀምበት ወይም ሳይወስደው የቀረ የእረፍት ግዜ ካለ ደግሞ ቢያንስ ከ80 ሰዓታት ያልበለጠ፤ ወደ ሚቀጥለው ዓመት እንዲተላለፍለት መፍቀድ ይገባቸዋል።
- ሰራተኞች በተከታታይ ለሶስት ቀናት የህመም ሆነ የደህንነት ጥበቃ ፈቃድ ሲወስዱ፤ አሰሪዎች ክሚመለከተው ሰው ወይም ባለስልጣን የፈቃድ መውሰጃቸው ምክንያት የሚገልጽ ወረቀት እንዲያመጡ አሰሪዎች ሊጠይቁ ይችላሉ።

### ይህንን የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ፈቃድ ምን ጉዳዮች ሲይጋጥሞት ነው ሊጠቀሙበት የሚችሉት?

የሚከተሉት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ የኢ-ኤስ-ኤስ-ቲ-(ESST) ፈቃድ መጠቀም ይቻላል፤

- የሰራተኛ ወይም የሰራተኛው የቤተሰብ አባል የአንጎል ወይም የአካል ህመም ሲያጋጥም ወይም እነኚህን ለመከላከል እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን
- በራስ ላይ ወይም በቤተሰብ አባል ላይ በተፈጸመ የቤተዘመድ ዓመጽ (domestic abuse) ወይም በግዴታ በሚደርግ ወሲባዊ ዓመጽ/ጥቃት (sexual assault) ወይም አንድ ሰው በሚያደርገው ተደጋጋሚ የመከታተል ጥቃት (stalking)፤ ከስራ መቅረት ሲያስፈልግ እና
- ሰራተኛው ወይም የሰራተኛው ቤተሰብ አባል የስራ ቦታ ወይም የትምህርት ቦታ በአየር ብከላ ወይም በህዝብ ላይ በደረሰ ድንገተኛ አደጋ ምክንያት ሲዘጋ



**የህመም ግዜ**

የአንጎል ወይም የአካል ህመም፤ እነሱን ለመታከም ወይም ለማስወገድ የሚደረግ የማስወገጃ እንክብካቤ



**የደህንነት ጥበቃ ግዜ**

የቤተዘመድ ዓመጽ ((domestic abuse)፣ የአስገድዶ መዳፈር ወይም ወሲባዊ ጥቃት (sexual assault) ወይም አንድ ሰው የሚያደርገው ተደጋጋሚ የመከታተል ጥቃት (stalking)፤ የመሳሰሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ

ህዳር (November) 2023

DEPARTMENT OF LABOR AND INDUSTRY

651-284-5075 • 800-342-5354 • esst.dli@state.mn.us • dli.mn.gov/sick-leave

ማስታወሻ: ይህ የሚኖሶታ ህግ አጭር መግለጫ ነው። ዓላማውም እንደ መመርያ እንዲወሰድ እንጂ የሚኖሶታን ህጎች የሚተካ ነው ተብሎ እንዲወሰድ አይደለም።